# ኢትዮጵያችን

*ወቅታዊ አተታ*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 6 ቁጥር 2 የካቲት 5 ቀን 2015 ዓ.ም.


## “ሕይወት ለሀገር”

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በየጊዜው የደረሰባትን እና የሚደርስባትን መከራ በአምላክ ቸርነት፣ በአባቶች እና በምዕመናኑ ጥንካሬና እምነት እየተወጣች ዛሬ ላይ ደርሳለች።ጥር 14 ቀን 2015 ዓ.ም. ሕጋዊውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቅዱስ ሲኖዶስን በመናቅ ሌላ የዘር እና የክልል ሲኖዶስ በህገወጥ መልኩ ሲሰየም “ከሰደበኝ ደግሞ የነገረኝ” እንዲሉ የጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም. ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ላይ ያሳዩት ተጨማሪ ንቀትና ትዕቢት የተሞላበት መግለጫ የተሰጣቸውን የውሃ ልክ በመዝለል ከፈጣሪ ተጋጩ። እምነት ማለት ምን እንደሆነ የሚማሩ ከሆነ እስኪያንገሸግሻቸው ድረስ የአባቶቻችን ጥንካሬ፣ የምዕመናኑን አንድነት ከሰሞኑ እንቅስቃሴ ሊገነዘቡት ይገባል።ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀደምት አምባገነን ገዥዎች ያስለመዱንን አምባገነናዊ መግለጫ ከማክተልተል ባለፈ መልኩ ምዕመናን በጥይት ቢቆሉ፣ ቢደበደቡ አካል ጉዳተኛ ቢያስደርጉ፣ ቀሳውስት በጥፊ ቢጠፈጠፉ፣ ልብሳቸውን አስወልቀው ቢቀጠቅጧቸው ወይ ፍንክች! ካለው ሕዝብ ያገኙት “ድል” ቢኖር ፍርሃት፣ መርበትበት፣ የአገዛዙ መናጋት፣ በሠራዊቱ ውስጥ “እኔም ለእምነቴ” ስሜቶች ለመሆኑ ቀጣይ ሂደቶች እንደሚመሰክሩ መገመት አያዳግትም።

የቤተ ክርስቲያኑ ሕግና መብቴ ይከበር ብላ በመላው ዓለም ቅዱስ አባቶቻችን ባስተላለፉት ጥሪ መሠረት “የሕዝብ ሙቀቱ አንድነቱ” እንዲሉ መንግሥትን ያነቃነቀ፣ ያርበተበተ እንቅስቃሴ ለአለፉት 15 ቀናት ሀገራችን አስተናግዳለች። እንቅስቃሴው በሌላ መልኩ በተለይ ላለፉት 5 ዓመታት በየቀኑ በአገዛዙና በጀሌዎቹ ስታስተናግድ የነበረውን የሰው ልጅ እልቂት ላይ በተለያዩ መገናኛ ዜዴዎች በተዘገበው መሠረት በሻሸመኔ 38፣ በወለቴ 1 ተጨማሪ ሕይወት አጥታለች። በየቀኑ አሁንም እየተደበደቡ እየታሰሩ ያሉ ምዕመናን እና ወጣቶች ቤቱ ይቁጠራቸው።

ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የካቲት 4 ቀን 2015 ዓ.ም. በተሰጠው መግለጫ መሠረት ከአገዛዙ ጋር በተደረሰው ስምምነት ሌላኛው ሕገወጡ ሲኖዶስ ስለተሠረዘ ታቅዶ የነበረው የዕሁድ የካቲት 5 ቀን 2015 ዓ.ም. ዓለም አቀፍ ትዕይንተ ምዕመናን/ሕዝብ ለተወሰነ ጊዜ መተላለፉ ተገልጿል።እንደ አንድ ፖለቲከኛ ቤተ ክህነት ይህንን ውሳኔ ስታስተላልፍ እውን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይቅርታ ጠይቀው ነውን? ሕይወታቸውን ያጡት ሰማዕታት ጉዳይስ? በየአካባቢው የወደሙትና የተቃጠሉት ቤተ ክርስቲያን ጉዳይስ? ቤተ ክርስቲያኗ የጀመረችው የክስ ጉዳይስ? ሌላም ሌላ ጥያቄዎች እጅግ ትንታኔ ሊሰጥባቸው ከማስቻሉም በላይ በአንዳንዶች የቅዱስ ሲኖደሱ ውሳኔ “የሽንፈት” ምልክት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

የሀገሪቷን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከት ዛሬ ሕዝባችን ከደረሰበት እጅግ የመረረ ሁኔታ፣ በየጊዜው እየረገፈ ያለውን የአማራ ዘር ስንመለከት፣ በጥቅሉ በብልጽግና የአምስት ዓመት አገዛዝ የደረሰበት መከራ ለመገላገል መፍትሄው የአገዛዙ መወገድ ብቻ ሳይሆን ዘርና ቋንቋን ተገን ያደረገ ሕገ መንግሥት ቦታውን በትውልድ ተሻጋሪ ኢትዮጵያዊ ሕገ መንግሥት ይቀየር ዘንድ ፍላጎት ያለው ኅብረተሰብ ምዕመናኑን ጨምሮ በዚህ ውሳኔ ቅር ቢሰኝ አይፈረድበትም። የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ሙቀቱ ፈልቷል፣ እምነቱን እንደሚፈልግ ሁሉ ሀገሩን ይፈልጋታል። እምነትና ሀገር ለኦርቶዶክስም ሆነ ለእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሲሆኑ በእምነቱ መሪ አባቶቹን ይከተላል፣ በሀገሩ ደግሞ አልተከሰቱም እንጂ ጠንካራ የፖለቲካ መሪዎችን ይሻል።

ንጉሣዊ አገዛዝ ያበቃበትን እንደ መነሻ ብናደርግ በትንሹ ለ50 ዓመታት መከራ ያልተለያት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የዛሬ 49 ዓመት "በአብ-ወልድ-መንፈስ ቅዱስ" ፈንታ "ማርክስ-ኤንግልስ-ሌኒን" ተዜሞባት ፓትሪያርኳን በግድያ አጥታለች። በቀጣይ የወያኔ/ህወሓት አገዛዝ የነበሩት ፓትርያርኳን ጨምሮ በመላው ዓለም ቤተ ክርስቲያኗም ሆኑ አባቶቻችን ከነታቦቱ ለስደት ሲበቁ "ወይ ጊዜ!" ቢያሰኘንም ዛሬ ላይ ሁነን ስናየው "ለበጎ ነበር" ያሰኛል። ዛሬ በመላው ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንኳን ልትፈርስ አድማሷን አስፍታ ዓለም አቀፋዊ ባህሪ እየያዘች መምጣት፣ ጅምር ቋንቋዋን ግዕዝ ዓለም እያጠናላት መሆኑን ስናይ የአምላክ ቸርነት ነው። አሜን! ይህንን ነው እንግዲህ የብልጽግናው አገዛዝ እና መሪ በክልል እና በዘር ሊሸነሽናት የተነሱት። ያገራችን ሰው "አልሰሜን ግባ በሉት" እንደሚለው ዘው ብለው ከፈጣሪ ጋር ግብ ግብ ጀምረዋል፤ በአራዳዎቹ ቋንቋ "ይመቻቸው!"።

በትንሹ በ60 ሚሊዮን የሚቆጠር ተከታይ ያላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት "ነግ በእኔ" ነውና ለዘመናት አብሮና ተከባብሮ የኖረው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮቻም ከጎኗ እንደሚሆኑ የሱማሌ ክልል አስተዳዳሪ ሙስጠፌ መሐመድ አቋም በቂ ምስክር ነው። ይህንን ታላቅ ቁጥር ያለው ሕዝብ ያንቀሳቀሰች ቤተ ክርስቲያን ከእምነቱ ባሻገር በአለው አገዛዝ ላይ የሕዝባችን መንገሽገሽ፣ በቃኝ ባይነት፣ አንድነቱን እና ሰላም ውሎ ማደርን ፈላጊነት ምልክት ነውና ይህንን እንቅስቃሴ ተገን አድርጎ በሀገር ቤት የምትንቀሳቀሱ ሕዝባዊ የፖለቲካ ድርጅቶች በፍርሃት ሳትዋጡ መሪነትን በመውሰድ ለድል ታበቁት ዘንድ ይጠበቅባችኋል። ይህን የተጋጋለ ሕዝባዊ መነሳሳት ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊነቷንና መብቷን ከማስከበር ባሻገር ስለማትገፋ ልትባንኑ ይገባል።

በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው በዐብይ አሕመድ የሚመራው የብልጽግና አገዛዝ አብቅቶለታል ግና ትግሉ መሪ ይፈልጋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለት አማራጭ ከፊቱ ተደቅኗል በየቀኑ ሳይሆን በየደቂቃው እየተጨፈጨፉ፣ እየታረዱ፣ እየታሰሩ፣ እየተደበደቡ ከሞት አይሻል ሕይወት መግፋት ወይም ከአለው አገዛዝ ጋር ተናንቆ ለድል መብቃት። "ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት አንዱን ግባ በለው" ነውና ሀገርን ለማዳን ቆርጦ የተነሳን ሕዝብ መርቶ ለድል ማብቃት ቆራጥነት የተሞሉ መሪዎች የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ ተደርሷል። "አንዱን ሞት ግባ" ላለ ሕዝብ ሊሰዋ ያልተዘጋጀ የፖለቲካ መሪ እንደተለመደው ትግሉን ትቶ የአገዛዙን ምክር ቤት ሲያደምቅ በግብታዊነት ለሚነሳው ሕዝባዊ አመጽ አምላክ መሪ ያዘጋጅለታል። አይ የዚያን ጊዜ ታዲያ አጨብጫቢውና አለሁ ባዩ ሲያሳፍር።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በዚህ 15 ቀን እንቅስቃሴ እንደ እምነቷ "ጥቁር ቀንን" አበርካታለች፣ ላልተወሰነ ጊዜ ቢተላለፍም "የመስዋት ቀን" አውጃለች፣ "ሃይማኖት ደምሥሬ" ብላለች፣ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሀገር መሆኗን አስመስክራ እምቅ ኃይሏን አሳይታለች። ይህን ጥንካሬዋን አናንቆ የወጣው የኦሮሙማ መግለጫ የመንግሥትን አቋም አንጸባራቂ ነውና መንግሥት አሁን በያዘው አቋም ጊዜ ገዝቶ ለሌላ ዕቅድ እንደሚዘጋጅ እንደ ፖለቲከኛ መገንዘብ አስፈላጊ ነውና ከመንግሥት ጋር ይደረግ የነበረው ውይይት እየተካሄደ ሚታሰሩ፣ ሚደበደቡ ነበሩ፤ አገዛዙ እድሜ ከሰጠው ዛሬም ነገም ይቀጥላል። በተለይ በቅርብ ሊካሄድ ለተያዘው የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ የተረጋጋ ለመምሰል ይፈልገዋልና "ቀን እባብ ያየ ማታ በልጥ ይደነብራል" ነውና የጥቅምት 18ቱን የዶር ዐብይ መግለጫ ያደመጠ ዳግም እንዳይታለል ልናስገነዝብ እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን መብት ጥያቄ ተገን አድርጎ በሀገራችን የተቀሰቀሰውን ሕዝባዊ ስሜት እንደጋለ ለማስቀጠል እና ለድል ለማብቃት በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑ የፖለቲካ ድርጅቶችን አካቶ፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ **"ሕይወት ለሀገር"** ግብረኃይል ይቋቋም ዘንድ ሃሳብ እናቀርባለን። የሚቋቋመው ግብረ ኃይል ዓለም አቀፋዊ ይዘትና ጥንካሬ ይኖረው ዘንድ ከመላው ዓለም/አህጉር በተውጣጡ ተወካዮች ተካተውበት በሀገር ቤት ከሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ምሁራን፣ የመገናኛ አውታሮች እና ሌሎችን ያካተት ዘንድ ቢመከርበት መልካም ነው።

ይህ ግብረኃይል ዋናው ተግባሩ አሁን የተነሳሳውን ሕዝባዊ እምቢተኝነት በመምራትና አቅጣጫ በማስያዝ ሊመከርበት የሚገባ ተልዕኮ፣ ዓላማና ራዕይ ቢኖረውም በጋራ ስምምነት ሊደረግበት የሚገባው ግን ***ያለው የብልጽግና አገዛዝ ከነዘረኛ ሕገ መንግሥቱ ተወግዶ፣ ለአለፉት 32 ዓመታት ከወያኔ/ህወሓት/ብልጽግና አገዛዝ በሀገራችን ለደረሰው የሰው ልጆች ሕይወት መቀጠፍ በተለይ ደግሞ በአለፉት 5 ዓመታት የብልጽግና አገዛዝ በጅምላ በአማራው ለደረሰውና እየተደረገ ላለው ጭፍጨፋ በተጨማሪ በአለፉት ሁለት ዓመታት በተከሰተው ጦርነት ለጠፋው የትግራይና ሌሎች ኅብረተሰብ ክፍሎች ህይወት ተጠያቂዎች ፍትህ ይመለከታቸው ዘንድ ማካተት ዋናው ተግባሩ መሆን ይኖርበታል።***

ተስማምቶ፣ ተከባብሮና ተመካክሮ ይህን ግብረኃይል ተግባራዊ አድርጎ መንቀሳቀስ ካልተቻለ ሕዝባዊ ትግሉ መቀጣጠሉ፣ ያለው አገዛዝ መውደቁ አይቀሬ ነውና ያለውን ክፍተት ሌላ ተረኛ ወይም የወታደር አገዛዝ ሊረከበው እንደሚችል ቢገመትም አስፈሪውን ስንቃኘው ደግሞ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የእርስበርስ ግጭት ውስጥ ተገብቶ ለከፋ ሀገራዊና ሕዝባዊ ጉዳት እንዳንዳረግ መፍጠን እንደሚገባ ልንጠቁም እንወዳለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች!

*ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ!*

**የካቲት 5 ቀን 2015 ዓ.ም. (February 12, 2023)**

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin